Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL



Summer RISE
Connecting Students to Careers

# Summer RISE 2026 Student Agreement
# ሠመር ራይዝ 2026 የተማሪ ስምምነት ሠነድ

Department of College and Career Readiness
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, Maryland 20850

## የወላጅ/የሞግዚት/የብቁ ተማሪ ስምምነት ሠነድ፦ PARENT/GUARDIAN/ELIGIBLE STUDENT CONSENT

የሠመር ራይዝ 2026 ፕሮግራም የተነደፈው በአሁኑ ወቅት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለሚማሩ ወጣት ጁንየሮች እና ሲንየሮች 2026 የሠመር ወቅት የሙያ ሥራ ትምህርት ልምድ እና እውቀት የሚገበዩበትን እድሎች ለማመቻቸት ነው። ለሠመር ራይዝ ፕሮግራም የምመዘገበው 2026-2027 የትምህርት ዓመት MCPS 11ኛ ክፍል ጁንየር ተማሪ ወይም 12ኛ ክፍል ሲንየር ተማሪ ስለምሆን ብቁ መሆኔን እርግጠኛ ስለሆንኩ ነው። ከወላጆቼ/ከአሳዳጊዬ ጋር ተስማምተን በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ለመሳተፍ ሙሉ ኃላፊነት እወስዳለሁ።

1. ከጁን 22, 2026 ጀምሮ እስከ ጁላይ 24, 2026 የሚካሄደው የሠመር ራይዝ መርሃ ግብር እስከ 5 ሳምንት ድረስ እንደሚካሄድ እና ቢያንስ 50 ሰአታት በተግባር መከታተል እንደሚኖርብኝ ተረድቻለሁ። በተመደብኩበት (የሙያ ልምድ ሰጪ) ቢዝነስ፣ ድርጅት፣ ኤጀንሲ፣ወይም አካል (“የሙያ ልምድ”) በሙያ ላይ የተመሰረተ በተግባር የመማር እድል፣ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊ በመሆን በቀን ከ 8 ሰአት ያልበለጠ እና በሳምንት ከ 40 ሰአት የማይበልጥ ጊዜ በሙያ ሥራ ልምምድ ቦታ እንደማሳልፍ ተረድቻለሁ። የሥራ ልምምዱ ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋቱ 7፡00 A.M. እስከ 6፡00 P.M. ሊካሄድ ይችላል። ከነዚህ ሰአታት ውጭ ለመሳተፍ ከመረጥኩ፣ ከቀኑ 9፡00 P.M. በኋላ መስራት የማልችል በመሆኑ፣ ለእኔ የስራ ልምምድ እድል ለመስጠት የሚቀበለኝ ተቋም ለሠመር ራይዝ ማስተባበሪያ ቢሮ በቅድሚያ ሊገለጽለት ይገባል። የእኔ መርሃ ግብር ከመጀመሩ አስቀድሞ በአስተናጋጁ ተቋም የሚወሰን ሲሆን ለእኔ ማረጋገጫ ይገለጽልኛል። የሚጠበቀውን የተማሪ አበል ለማግኘት በሙያ ክህሎት እና በፋይናንስ ትምህርት አውደ ጥናት ላይ 50 ሰአት መሳተፍ እና ማጠናቀቅ ይጠበቅብኛል። ከሙያ ልምድ ሰጪው አካል የሚመለከተ(ታቸ)ው የሥራ ባልደረባ(ዎች) (“Career Experience Host Designee(s)”) የሠመር ራይዝ ፕሮግራሙ ሲጠናቀቅ ተቀባይነት ያለው 50-ሠዓት የሙያ ሥራ ልምምድ ማረጋገጫ ይሰጣል።

2. እኔ በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ላይ ለመሳተፍ ከመረጥኩ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሥራ ልምምድ ፕሮግራምላይ ተሳታፊ ከሆንኩ፣ "Summer RISE" ካለው መስፈርቶች በተጨማሪ የሚከተሉትን ማድረግ እንዳለብኝ ተረድቻለሁ፦

    a. በሚከተለው አገናኝ ሊንክ ላይ የሚገኘውን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሥራ ልምምድ ፕሮግራም ስምምነት ማንበብ፣ መፈረም እና ማክበር፦ ww2.montgomeryschoolsmd.org/departments/forms/pdf/280-77.pdf፣
    b. ከጁን 22, 2026 እስከ ጁላይ 24, 2026 ማብቂያ ድረስ ጠቅላላ 75 ሰዓታትን ለማጠናቀቅ ተጨማሪ 25 ሰዓታትን ማሟላት፤
    c. የኢንተርንሺፕ አስተባባሪው ባዘጋጃቸው የቡድን ሴሚናሮች ሁሉም ላይ መሳተፍ፤
    d. በኢንተርንሺፕ ፕሮግራሙ ውስጥ የሚሳተፉበትን ሰዓቶች የአሰራር ሂደቱን በመከተል መመዝገብ እና በየጊዜው ሪፖርት ማድረግ፤
    e. ከፕሮግራሙ ጋር የተያያዙ ማናቸውንም ስጋቶችን ከኢንተርንሺፕ አስተባባሪው ጋር ያለምንም መዘግየት መነጋገር/ሪፖርት ማድረግ፤ እና
    f. በኢንተርንሺፕ አስተባባሪው የተሰጡትን ሁሉንም ስራዎች እና ፕሮጀክቶች ማጠናቀቅ። በኢንተርንሺፕ ፕሮግራሙ መጨረሻ ላይ የሥራ ምደባዎቹና ፕሮጀክቶቹ በሙያ ሥራ ልምድ አስተናጋጅ ሊገመገሙ ይችላሉ።

3. ለሠመር ራይዝ ፕሮግራም ከመመዝገቤ በፊት፣ "WORK-BASED LEARNING NAVIGATOR" በተግባር ስራ ላይ የተመሰረተ የትምህርት ዳሰሳ "CLEVER" አማካይነት ያሉትን አምስት ዋና የስራ ልምድ ፍላጎት ግምገማ ማድረግ እንደምችል ተረድቻለሁ፣ ይህም የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ቡድኔን በሙያ ልምድ ምደባ መርዳት ያስችላል።

4. በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ለመሳተፍ የወላጅ/አሳዳጊ ፈቃድን ማረጋገጥ እና ሠመር ራይዝ ከመጀመሩ በፊት ስለ ቨርቹዋል የሙያ ክህሎት የሚሰጠውን መግለጫ መከታተል እንደሚጠበቅብኝ ተረድቻለሁ። መግለጫ ሲሰጥ መከታተል ያለብኝ ከሚያስፈልጉት የፕሮግራም ሰዓቶች በተጨማሪ ነው። የስልጠናው ዝርዝር በኢ-ሜይል እንደሚላክልኝ ተገልጾልኛል።

5 እኔ በአካል የሙያ ልምምድ ማድረግ ካለብኝ፥ የሙያ ልምምድ እስከምወስድበት ቦታ ድረስ የመጓጓዣ ኃላፊነቱ የራሴ መሆኑን ተገንዝቤአለሁ። (5–18 እድሜ) ያላቸው ተማሪዎች በሙሉ በሞንትጎመሪ ካውንቲ "Youth Cruiser SmarTrip card" በመያዝ "Ride On"፣ "Ride On Flex" እና አንዳንድ ሜትሮባስ "Metrobus" መስመሮችን በነፃ ለመጠቀም ይችላሉ። የስማርት ትሪፕ ካርዶች "SmarTrip cards" ማመልከቻ በትምህርት ቤቱ እና በሌሎች ቦታዎችም ይገኛል። "Youth Cruiser SmarTrip" ካርድ ስለማግኘት የበለጠ መረጃ ለማግኘት የኮሌጅ/የሙያ ስራ መረጃ አስተባባሪዎን ያነጋግሩ እና/ወይም የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትራንስፖርት መምሪያ ድረ ገጽ www.montgomerycountymd.gov/DOT-Transit/kidsridefree/ ይጎብኙ።

6. <u>የሙያ ልምምድ ምደባ የሚደረገው በእኔ የሙያ ፍላጎት፣ የመኖርያ አካባቢ፣ በአካል፤ እና/ወይም ቨርቹወል ምርጫዬን መሠረት በማድረግ ስለሚሆን እንደመገኘቱ ሁኔታ የሚወሰን መሆኑን ተረድቻለሁ።</u>

7. <u>የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ያልሆነ የግል ኢሜይል አድራሻ መፍጠር እና ለሠመር ራይዝ ፕሮግራም እና የስራ ልምምድ እንዳደርግ ለሚቀበለኝ አካል ማሳወቅ እንዳለብኝ ተረድቻለሁ። የሠመር ራይዝ ፕሮግራምን በተመለከተ ወቅታዊ መረጃዎች ወደዚህ ኢሜይል አድራሻ ይላካሉ፥ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ያልሆነውን እና ከ MCPS የሚላኩልኝን ኢሜሎቼን በየእለቱ ማየት እንዳለብኝ ከሠመር ራይዝ ቢሮ ተገልጾልኛል።</u>

8. <u>የእኔን መርኃግብር በሚመለከት ከሙያ ልምምድ ሰጪ የሚመለከተው ሠራተኛ ወይም ተወካይ (my "Career Experience Host Designee(s)") ጋር በቀጥታ የማስተባበር ኃላፊነት እንዳለብኝ ተረድቻለሁ።</u>

9. በጥሩ ሁኔታ ለመከታተል፥ ጥሩ ስነምግባር፥ ትክክለኛነት፥ ሥነ ሥርዓት መጠበቅና ማክበር፥ በፍጥነት መሥራት፥ አስተዋይነት፥ ተገቢ አለባበስ፥ እና አግባብነት ባለው የቢዝነስ ስነ-ምግባር እና ቨርቹወል የምሳተፍ ከሆነ፣ ቪድኦ ላይ መሆን እንደሚጠበቅብኝ ተገንዝቤአለሁ/ተስማምቻለሁ። በእኔ የስራ ልምምድ ተቀባይ/ተወካይ ሊፈቱ የማይችሉ ጉዳዮች ካጋጠሙኝ ወይም ስጋቶች ካሉኝ፣ የእኔን የሠመር ራይዝ አስተማሪ አገናኝ ወይም MCPS Summer RISE Program office summer-rise@ mcpsmd.org ወይም 240-740-5599 በመደወል ማነጋገር እችላለሁ።

10. በአካል በተገኘ የስራ ልምምድ ለመሳተፍ ከመረጥኩ፣ የእኔ የሠመር ራይዝ አስተማሪ ተባባሪ/ረዳት ወይም የሠመር ራይዝ ሰራተኞች የእኔን የሥራ ልምምድ በርቀት የመቆጣጠር አማራጭ እንደሚኖራቸው ተረድቻለሁ።

11. እኔን የስራ ልምምድ እንዳደርግ የሚቀበለኝ ተቋም ማጣራት እና ክትባቶችን ጨምሮ ሌሎች ተጨማሪ መስፈርቶች ለኖሩትእንደሚችል ተረድቻለሁ። ጁን 22 የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ከመጀመሩ በፊት ማንኛውንም ተጨማሪ የማጣሪያ መስፈርቶችን ለማሟላት ከስራ ልምድ አስተናጋጅ ወይም ተወካይ ጋር በቀጥታ መስራት እንደሚጠበቅብኝ እና ኃላፊነቱ የራሴ መሆኑን ተገንዝቤአለሁ። የሥራ ሙያ ልምድ የሚሰጠኝን ድርጅት/አስተናጋጅ መስፈርቶች ማሟላት ካልቻልኩ፣ ከተገኘ ሌላ እድል እስከሚሰጠኝ እጠብቃለሁ።

12. በአካል እየተገኘሁ በሰመር ራይዝ ፕሮግራም የሥራ ልምድ ለማግኘት ከተሳተፍኩ እና ከኮቪድ-19 ጋር የተያያዘ ማናቸውም አይነት ገደብ ቢኖር በራሴ ፍላጎትና በወላጅ/በአሳዳጊ ፍቃድ ስለምሳተፍ ገደቦቹን የማክበር ኃላፊነት እንዳለብኝ በመረዳት ተስማምቻለሁ። በተቻለ መጠን፣ የሙያ ልምድ ተቀባይ አስተናጋጆች ተወካይ(ዮች) በሞንትጎመሪ ካውንቲ አስተዳደር እና በ MCPS የተቀመጡትን የኮቪድ-19 ፕሮቶኮሎች መከተል አለባቸው። ለኮቪድ-19 ለተጋለጠ(ች) ተማሪ MCPS ምንም አይነት ሃላፊነት እንደማይወስድ ግንዛቤ ተወስዷል።

13. የሥራ ልምድ ለሚሰጠኝ ድርጅት/my Career Experience Host ተቀጣሪ አለመሆኔን። የሥራ ልምድ የሚሰጠኝ ድርጅት ከሠመር ራይዝ ተሳታፊዎች ወዲያውኑ የሚያገኘው ምንም አይነት ጥቅም አይኖርም፣ እናም አንዳንዴ ሥራቸው እንኳ ሊስተጓጎል ይችላል። በእኔ የስራ ልምምድ አስተናጋጅ ስራዎች ላይ በቀጥታ እንደማልሳተፍ ወይም በመደበኛነት ወይም በቀጣይነት ስራ እንደማልሰራ (ፋይል ማደራጀት፣ ሌላ የፅህፈት ስራ ወይም ደንበኞችን ማስተናገድ) በመሳሰሉት ስራዎች ላይ እንደማልሳተፍ ተረድቻለሁ። ለእኔ የሙያ ልምምድ የሚሰጠኝ ተወካይ የቢዝነስ/የድርጅቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴዎች የሚመለከት መግለጫ ይሰጡኛል፥ የእኔን ሚና፥ ኃላፊነቶች፥ እና ለቢዝነሱ/ለድርጅቱ ማክናወን ያለብኝን ተግባሮች ያስተምሩኛል። ሥራ አስፈጻሚው(ዋ) ወይም ማኔጀር በሚሠራው ሥራ ዉጤታማ በሆነ መንገድ ለመከወን የሚጠቀምበትን ስልት፣ ጥራት፣ ክህሎት፣ እና እውቀትን በጥልቀት በመሻት እነዚህን ተግባራት እፈጽማለሁ። በበርካታ የሥራ ቅጥር አካባቢዎች መጠቀም የምችለዉን ሙያ ለመማር እድል እንደሚኖረኝ ተረድቻለሁ።

14. ስለ እኔ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሞክሮ ቅድመ ዳሰሳ እና የፕሮግራም መጨረሻ ዳሰሳ ሪፖርት ለማቅረብ ተስማምቻለሁ።

15. የገንዘብ ድጋፍ/ፈንድ ከተገኘ፣ ለፕሮግራሙ የወጪ ማካካሻ አበል እንደሚሰጠኝ በመገንዘብ ተስማምቻለሁ። አበሉ የሚሰጠኝ ፕሮግራሙን በተሳካ ሁኔታ ከጨረስኩ በኋላ ነው። የሠመር ራይዝ ፕሮግራምን እንደጨረስኩ MCPS ከወላጅ/ከአሳዳጊ ፍቃድ ከተሰጠ በኋላ የአበል ቼክ ለማዘጋጀት ለሚያስተዳድረው ባንክን የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ስሜን ያስተላልፋል። የድጎማ ቼኩ ክፍያ የሚፈፀመው በቂ የገንዘብ ድጋፍ መገኘት ላይ የተመሰረተ እና ዝቅተኛው 50-ሰአት መስፈርት ተሟልቶ መጠናቀቁ በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ጽ/ቤት ከተረጋገጠ በኋላ ፕሮግራሙ እስኪጠናቀቅ ድረስ እንደማይከፈል ተረድቻለሁ። ቼክ ለመውሰድ በጋራ የሚመች ጊዜ አስቀድሞ ቀጠሮ ማስያዝ ያስፈልጋል። የተማሪ ክፍያን ሂደት በተመለከተ የእኔን ሠመር ራይዝ አስተማሪ አገናኝ ወይም Summer RISE Program office በዚህ ኢሜል summer-rise@mcpsmd.org ማግኘት እችላለሁ፥ ወይም 240-740-5599 በመደወል ጥያቄዎቼን ማቅረብ እችላለሁ።

16. በሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" መሣተፌ የሙያ ልምምድ ካደረኩበት ተቋም (my Career Experience Host) ሥራ የማያስጠኝ መሆኑን እና በሠራተኝነት ለመቀጠር መጠበቅ እንደሌለብኝ ተረድቻለሁ።

17. የሠመር ራይዝ ፕሮግራም በምሳተፍበት ወቅት ቪዲዮ ለመቀረጽ፣ ፎቶግራፍ ለመነሳት፣ እና/ወይም ለመቀረጽ ("ፎቶ እና ቪዲዮ ለመልቀቅ") ከወላጅ/አሳዳጊ ፈቃድ ማግኘት እንደሚያስፈልገኝ ተረድቻለሁ ምስሎቹ እና/ወይም ሪኮርዶቹ ስለ ሠመር ራይዝ ለማስተዋወቅ ተጨማሪ ፈቃድ ሳይጠየቅ ለተለያዩ ዓላማዎች ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ተስማምቻለሁ። በእነዚህ አጠቃቀሞች ምክንያት ምንም ክፍያ እንደማይሰጠኝ እና ምስሎቹ፣ ቪድዎቹ፣ ሪኮርዶቹ፣ እንዲሁም ማናቸውም በዚህ ምክንያት የሚፈጠሩ ሥራዎች ባለቤትነቱ የ MCPS መሆኑን እገነዘባለሁ። ወላጆቼ/አሳዳጊዬ ለፎቶ እና ቪዲዮ መነሳት እና መልቀቅ ፈቃደኛ ባይፈቅዱልኝም በሠመር ራይዝ ፕሮግራም መሳተፍ እንደምችል ተረድቻለሁ።

18. MCPS የሠመር ራይዝ ፕሮግራምን ለሚያስተዳድረው MCPS በሥራ ላይ የተመሠረተ ትምህርት ቢሮ፣ ነፃ ወይም ቅናሽ ዋጋ ያላቸውን ምግቦች (FARMS) መረጃ እንዲሰጥ የወላጅ/የአሳዳጊ ፈቃድ እንደሚያስፈልገኝ ተረድቻለሁ። በስራ ላይ የተመሰረተ ትምህርት ቢሮ የተማሪዎችን FARMS መረጃ ለተማሪዎች ድጋፍ እና ለጠቅላላ ሪፖርት ዓላማ እንደ መረጃ መጠቀም ይፈልጋል። ይህ የተማሪ መረጃ "MCPS Work-Based Learning office" ውጭ ላሉ ሰራተኞች አይጋራም። በተጨማሪም ወላጆቼ/አሳዳጊዬ FAARMS ሁኔታዬን መረጃ ለማጋራት ፈቃደኛ ባይሆኑም እንኳ በሠመር ራይዝ ፕሮግራም መሳተፍ እንደሚቻል ተረድቻለሁ።

19. የእኔ የሥራ ልምምድ ተቀባይ/ተወካይ ስለ እኔ የሥራ ልምምድ ተሳትፎ ከ MCPS ጋር መረጃ እንደሚለዋወጡ ተረድቻለሁ። የእኔ የስራ ልምምድ አስተናጋጅ ወይም ተወካይ የሠመር ራይዝ ተሳታፊዎችን የሚመለከት ምንም አይነት መረጃ ለሦስተኛ ወገን አያጋራም።

20. ይህን የስምምነት ውል፣ በስራ ልምድ አስተናጋጅ መሥሪያ ቤት የተቀመጡትን ደንቦች እና መመሪያዎች፣ወይም ማንኛውም ሌላ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ህጎችን ማክበር ካልቻልኩ፣ከሠመር ራይዝ ፕሮግራም መሠረዝ እና ድጎማውን ለመቀበል ብቁ እንደማልሆን ተረድቻለሁ።

21. ስለ ሙያ ልምምድ ማንኛውም ስጋት ካለኝ፣ ወዲያውኑ ለሠመር ራይዝ ትምህርት አገናኝ ወይም ለሠመር ራይዝ ፕሮግራም ቢሮ summer-rise@mcpsmd.org ወይም በስልክ ቁጥር 240-740-5599 በመደወል ሪፖርት ማድረግ እንዳለብኝ ተረድቻለሁ።

"ሠመር ራይዝ 2026 የተማሪ ስምምነት" ለማመልከት የተማሪ የስምምነት ሠነድ በመመዝገቢያ ቅጹ ላይ ባለው ምልክት ይገለጻል፥እናም ይህ በኤክትሮኒክስ የሚቀርበው ስምምነት እና የኤሌክትሮኒክስ ፊርማ ከግል የጽሑፍ ፊርማ ጋር እኩል መሆኑን እንደተገነዘበ) ይቆጠራል።